Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# የድሬ ዳዋ ከተማ መልከ ብዙ ውዝግቦት

### የሰላም ምርምር ተቋም/ሪፍት ቫሊ ኢንስቲትዩት፣ በኢትዮጵያ የሚታዩ የከተማ ውዝግቦች ጥናት ፕሮጀክት

## ማጠቃለያ

ከኢትዮጵያ ከተሞች በሕዝብ ብዛት ሁለተኛ የሆነችው ድሬ ዳዋ ከተማ፣ በምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል የብሔረሰቦች፣ የቋንቋ እና የኃይማኖት ብዝኃነት የሚገለጥባት ማዕከል መሆኗ ይታወቃል። ነገር ግን በ2010 የተደረገውን ሀገራዊ የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ፣ በርካታ ጎብኚዎችን የምታስተናግደውና በሰላሟ የምትታወቀው ከተማ ለሁለት ዓመታት የብሔር እና የኃይማኖት ግጭቶችን አስተናግዳለች። ግጭቶቹም በከተማዋ በሚገኙ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እና ኃይማኖቶች መካከል ያለውን ውጥረት አሳይተዋል፡፡

ከ2012 እስከ 2015 እንዲሁም ይህ ጥናት እስከተካሔደበት ድረስ ባሉ ጊዜያት ግን ከተማዋ ወደ ቀድሞ መረጋጋቷ ተመልሳለች ። ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በተለየ አንፃራዊ ሰላም እንዲሰፍን በርካታ ለውጦች ቢደረጉም፣ በዋነኛነት ሁለት ጉዳዮች ጉልህ ሚና ነበራቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ መንግሥት በግጭቶቹ ግንባር ቀደም ተዋናይ የሆኑ ኃይሎች ላይ ሕግ የማስከበር ዕርምጃ መውሰዱ እና ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች ላይ የተወሰደዉ እርምጃ ሲሆን፤ ሁለተኛው የከተማ አስተዳደሩ የአመራር ለውጥ፥ በተለይ የከተማዋን ተወላጆች በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ መካተታቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ፥ አሁንም መልስ የሚሹ የተለያዩ ቡድኖች ያሏቸው ፍላጎቶች የሥጋት ምንጭ ሆነዉ ቀጥለዋል።

በድሬ ዳዋ የሚታየው ውዝግብ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ባለድርሻ አካላት ተዋናይ የሆኑበት ነው። ዋነኛ ተዋናዮቹ የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ የፌደራል መንግሥት፣ የኦሮሚያ ክልል፣ የሶማሊ ክልል፣ በሶማሊ ክልል ውስጥ ያለው የሺኒሌ ዞን፣ የሱማሌ ኡጋሶች (የጎሳ መሪዎች)፣ የኦሮሞ አባ ገዳዎች እና የድሬ ዳዋ ከተማ የኃይማኖት ጉባኤ አባላት ናቸው።

በተጨማሪም የከተማዋ ነዋሪዎች እና እንደ ዕድር እና ዕቁብ ያሉ ማኅበራዊ ተቋማትም በእጅጉ ይሳተፋሉ።

በኢኮኖሚው ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ተዋናዮች የድሬ ዳዋ ኢንደስትሪ ፓርክ እና የድሬዳዋ የነፃ ንግድ ቀጠና፣ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣ የመሬትና ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ የባጃጅ አሽከርካሪዎች፣ የጉልበት ሠራተኞች ማኅበራት (ጫኝና አውራጆች)፣ አነስተኛ የንግድ ተቋማት፣ መደበኛ ያልሆኑ ነጋዴዎች እና ኮንትሮባንድ ነጋዴዎችን ያካትታሉ። ውዝግቦቹ አምስት ዋና ዋና መንስዔዎች አሏቸው። የመጀመሪያው መንስዔ ዓመታትን ያስቆጠረውና አሁንም የሚታየው በኦሮሞ እና በሶማሊ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ያለው የከተማዋ የባለቤትነት እና የይገባኛል ጥያቄ ነው። የድሬደዋ ከተማ ቻርተር በከተማዋ ላይ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልል መካከል የነበረዉን አለመግባባት ለመፍታት ሲባል የተደነገገ ቢሆንም፤ በሁለቱ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ስለ ከተማዋ ያሉ ልዩነቶች ግን ቀጥለዋል። ይህም በዋናነት ከአስተዳደር ወሰኖች፣ ከመሬት አጠቃቀም እና አሰፋፈር ጋር በተያያዙ ግጭቶች ላይ ይስተዋላል።

ሁለተኛ፣ በከተማው ውስጥ በዋና ዋና የኃይማኖት ቡድኖች ከዚ በፊት የነበረዉ ውዝግብ፤ በቡድኖች መካከል ባለው ግንኙነት እና የአሰፋፈር ዘይቤ ላይ ተፅዕኖ ኣሳድሯል።

በ2011 እና 2012 በነበረው ሁነታ አካታች የግጭት አፈታት እና የዕርቀ ሰላም ሂደቶች ባለመኖራቸው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው አዲስ የአሰፋፈር ዘይቤ ወጥ ጉርብትና እንዲፈጠር አድርጓል። ይህ አዝማሚያ የቡድኖችን መስተጋብር የሚገድብ እና ያሉትን ልዩነቶች በይበልጥ የሚያሰፋ ነው። ይህም በተለያዩ ብሔረሰቦች ወይም ኃይማኖቶች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶቸ ብዙ ተዋናዮችን ወደ ሚያሳትፉና ማንነትን መሠረት ወዳደረጉ ግጭቶች እነዲሸጋገሩ ያደርጋል።

ሦስተኛ፤ ቋንቋ፣ ባህል እና የሕዝብ መሰብሰቢ ስፍራዎች ዙርያም አንዳንድ ውዝግቦች ተከስተዋል። ። አፋን ኦሮሞ የከተማ አስተዳደሩ ይፋዊ የሥራ ቋንቋ አለመሆኑ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ የባህል ዕድገትን እና የትምህርት ዕድሎችን ይገድባል። በዚህም የተነሳ የኦሮሞ ማኅበረሰብ ቋንቋው መደበኛ እውቅና እንዲሰጠው መጠየቁን ቀጥሏል። ከዚህ ጋር ተያይዞም በከተማዋ የሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ላይ የሚታዩ የኦሮሞ ብሔር እሴቶችን የሚወክሉ ምልክቶች በሌሎች ብሔረሰቦች ዘንድ ጥርጣሬን ሲፈጥሩ ይስተዋላል።

በሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ላይ የሚታየው ውዝግብ አንድ ማሳያ ሊሆን የሚችል አንዱ ጉዳይ በቅርቡ የሚሊኒየም ፓርክ ስያሜ ወደ ታዋቂው የአፋን ኦሮሞ ሙዚቀኛ አሊ ቢራ ፓርክ መቀየሩ ነው። ይህ የከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ በአንዳንድ የዚህ ጥናት ታሳታፊዎች ዘንድ እርምጃው የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች በድሬ ዳዋ ላይ የባለቤትነት ጥያቄያቸውን እንዲያፀኑ ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለው ስላሰቡ ፍርሃትን ይፈጥርባቸዋል። አራተኛው የውዝግብ ገጽታ በከተማዋ ነዋሪዎች እና በከተማ አስተዳደሩ መካከል ያለው አለመግባባት ነው። ነዋሪዎቹ የድሬ ዳዋ ከተማ ቻርተር እና መደበኛ ያልሆነው የ40:40:20 የሥልጣን ክፍፍል ስምምነት የተመጣጠነ ውክልና የማግኘት መብታቸው መንፈጉን ይገልጻሉ። ይህንን ይበልጥ የሚያሳየው በከተማና በገጠር ቀበሌዎች መካከል ያለው የምክር ቤት መቀመጫ ክፍፍል ተመጣጣኝ አለመሆኑ እና በከተማው አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ የኃይማኖት ቡድኖች እና ነዋሪዎች እኩል ውክልና አለመኖሩ ነው።

አምስተኛው፤ ድሬ ዳዋ ከኦሮሚያ ክልል ሐረርጌ ዞኖች እና ከሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚመጡ የኢኮኖሚ ፍልሰተኞች መጨመራቸው እና እነዚህ ፍልሰተኞች በከተማዋ ላሉ ውሱን የሥራ ዕድሎች ከአካባቢው ወጣቶች ጋር በመፎካከራቸው ከተማዋን ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ጥሏታል። ፍልሰቱ ከአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም እና ከወንጀል መጨመር ጋርም ተያያዥነት አለው። በአንዳንድ የከተማዋ አካባቢዎች መደበኛ ያልሆኑ አሰፋፈሮች የጸጥታ ችግርንም እየፈጠሩ ይገኛሉ። እነዚህን ፍልሰተኞች ከመኖሪያ ቤታቸው በኃይል የማፈናቀል ሙከራ ግጭት ሊፈጥር ስለሚችል ለከተማ አስተዳደሩ ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

እነዚህን አምስት የውዝግብ መንስዔዎችን መመርመር፥ እንዲሁም የዋና ዋና ተዋናዮቹን ማንነት እና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት በጥልቀት መረዳት ለዘላቂ መፍትሔ ወሳኝ ነው። ይህንን መረዳት በከተማው የሚታዩ ችግሮችን ለማረም፣ የግጭት መንስዔ ልዩነቶችን በመለየት ለፖሊሲ አውጪዎች ማሳወቅ እና በድሬ ዳዋ ሊፈጠር የሚችልን አካባቢያዊ ውጥረት እንዲሁም የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር ያስችላል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ ኢትዮጵያ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ግጭቶች እያስተናገደች ሲሆን፣ በጥር 2016 በኢትዮጵያ እና በሶማሊላንድ መንግሥታት መካከል የተፈረመውን ስምምነትን ተከትሎ በአከባቢው ውጥረቶች ተስተዉለዋል። በድሬ ዳዋ ከተማ የሚከሰቱ ግጭቶችና ውጥረቶች ወደ አጎራባች ክልሎችና አገሮች ሲሸጋገሩ እንደሚችሉ ሁሉ፣ እንዲህ ያሉ ትላልቅ ቀጣናዊ ጉዳዮች በከተማዋ የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የማሳደር አቅም እንዳላቸው እሙን ነው።

በድሬ ዳዋ፣ በምስራቅ ኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ሰላምን ለማስፈን እና ሁከትን ለማስወገድ እነዚህን እርስ በርስ የተቆራኙ መስተጋብሮችን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።

## የኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም

ይህ ሪፖርት ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም የተጻፈ ሲሆን፥ ውዝግብ የሚታይባቸው የከተማ ስፍራዎችን የተመለከቱ ጭብጦች የተዳሰሱበት የዕውቀት ለሰላም (Knowledge for Peace) ምርምሮች አካል ነው። የሰላም ምርምር ተቋም ገለልተኛ የሆነ ወቅታዊ የሰላምና የግጭት ትንታኔዎችን ከኢትዮጵያዊ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በማቀናጀት በአገሪቱ ግጭት አገናዛቢ የሆነ የፖሊሲና ፕሮግራም ቀረጻ እንዲኖር ያግዛል። ተቋሙ በሪፍት ቫሊ ኢንስቲትዩት (አር ቪ አይ) የሚተዳደር ሲሆን፥ በእንግሊዝ መንግሥት ድጋፍ ይደረግለታል።

## የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም

የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም በምስራቅና ማዕከላዊ አፍሪካ የሚሠራ ሲሆን፣ አገር በቀል ዕውቀቶች በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። የቅጂ መብት © የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም 2017። ይህ ሪፖርት በክሪኤቲቭ ኮመንስ አሠራር መሠረት ለንግድ ሳልሆነ ዓላማ ይዘቱ ሳይቀየር መጠቀም እንዲቻል ተፈቅዶ የታተመ ነው (CC BY-NC-ND 4.0)።

Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility